

የመዓዊያ ፀጉር

አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምር መምህር ነበር። አንድ ቀን በማስተማር ላይ እያለ ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ቸልተኛ እንደሆኑና ወደ ኋላ እንደቀሩ ተረዳ። ስለዚህ ትምህርት ሊሰጣቸው ወሰነ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ክፍል ውስጥ እንደገባ ወዲያውኑ "ተማሪዎች እስከርቢቶና ወረቀት አውጡ" አላቸው።

"ለምን?" ሲሉ ተማሪዎቹ ጠየቁ።

"ድንገተኛ ፈተና አላችሁ" አላቸው። ተማሪዎቹ ተንጫጫ። አንድ በረብሻው የሚታወቅ ግዙፍ ተማሪ "መምህር አሁን ፈተና መፈተን አንፈልግም። አጥንተን እንኳ መስራት አልቻልንም። ሳናጠና እንዴት ልንሆን ነው?" በማለት ጮኸ። ተማሪው በጩኸት ሲናገር መምህሩ ተቆጣ። "እናንተ በፈለጋችሁት አይደለም ሁሉም ነገር የሚሆነው። ይገባችኋል? ፈተናውን መፈተን አለባችሁ። ካልፈለጋችሁ ክፍሉን ለቃችሁ ውጡ!" አለ።

ተማሪውም፡- "አንተ ራስህ ውጣ" አለው። አስተማሪው "አንተ ስድ ነህ። ባለጌ" እያለ ይሰድበው ጀመር። ተማሪው ከመቀመጫው ተነሳና እዚህ ላይ መጥቀስ የማልፈልገውን ተግባር ፈፀመ። ነገሩ ወደ ትምህርት ቤቱ አስተዳደር ደረሰ። ተማሪው ውጤት ተቀነሰበት። በድጋሚ ምንም ዓይነት መጥፎ ባህሪ ላያሳይ ፈረመ። በዚያ ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ አስተማሪው ስለደረሰበት ነገር ማውራት ጀመረ። እሱን ባዩ ቁጥር ይንሾካሾካሉ። በዚህ የተማረረው አስተማሪ ትምህርት ቤቱን በመልቀቅ ሌላ ትምህርት ቤት ገባ።

ሌላኛው አስተማሪ አንድ ቀን ከፍል ውስጥ ገባና "እባካችሁ እስከርቢቶና ወረቀት አውጡ። ድንገተኛ ፈተና አላችሁ" አለ። አንድ ተማሪ ተነሳና "መምህር! አንተ በፈለግከው ጊዜ ፈተና ልትፈትነን አትችልም" አለው። መምህሩ አስተዋይ ነበር። ግትር ለሆነ ሰው ግትር ምላሽ መስጠት እንደማያስፈልግ ያውቃል። ተማሪውን በፈገግታ እየተመለከተ "ኻሊድ ፈተናውን መፈተን አትፈልግም?" ሲል ጠየቀው።

"አዎ አልፈልግም" አለ።

በተረጋጋ ድምጽ "ፈተና አልፈተንም ያለ ተማሪ በትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይቀጣል" አለውና ጥያቄዎቹን መዘርዘር ጀመረ።

"ጥያቄ ቁጥር አንድ..."

ያ ተማሪ መነጫነጩን ቀጥሏል። "ነግሬሃለሁ መምህር እኔ ይሆንን ፈተና መፈተን አልፈልግም" አለ። መምህሩ አሁንም በፈገግታ እየተመለከተው "ፈተናውን እንድትፈተን አላስገድድህም? አንተ ህፃን ልጅ አይደለህም። ኃላፊነቱን ወስደህ መተው ትችላለህ" አለው። ተማሪው አስተማሪውን ማበሳጨት እንደሌለበት ተረዳና ፀጥ አለ። ወረቀትና እስከርቢቶ አውጥቶ ጥያቄዎቹን መፃፍ ጀመረ። ባሳየው መጥፎ ባህሪም በትምህርት ቤቱ አስተዳደር የዲሲፕሊን ቅጣት ተቀጣ። ይሆን ታሪክ ሳስታውስ ሰዎች የተለያዩ ሁኔታዎችን ለማስተናገድ ያላቸው ችሎታ የተለያዬ መሆኑን ተረድቻለሁ። አንዳንዶቹ ችግርን በቀላሉ ሲፈቱ ሌሎቹ የባሰ ያወሳስቡታል። ግትር የሆነን ሰው ግትር በሆነ መልኩ መቅረብ ውጤቱ እሳት መፍጠር ነው። እሳትን በእሳት ማጥፋት እሳትን መጨመር ነው። ቅዝቃዜንም በቀዝቃዛ ነገር ማስቆም አይቻልም።

ስለዚህ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ያለው ግንኙነት ልክ እንደ ሙዓዊያ የፀጉር ዘለላ መሆን አለበት። ሙአዊያ በአስተዳዳሪነት ሃያ ዓመት በኸሊፋነት ሃያ ዓመት እንዴት ልትቆይ ቻልክ ተብሎ ሲጠየቅ "በእኔና በህዝቦቼ መካከል አንድ የፀጉር ዘለላ አስቀምጫለሁ። ከአንዱ ጫፍ እኔ ስይዝ ሌላኛውን ጫፍ እነሱ ይዘዋል። እነሱ ሳብ ሲያደርጉት ፀጉሩ እንዳይበጠስ እኔ ለቀቅ አደርገዋለሁ። እነሱ ለቀቅ ሲያደርጉት ደግሞ እኔ ሳብ አደርገዋለሁ" ሲል መልሷል። ሙዓዊያ አላህ ይርሀመውና ምን ዓይነት ብልህ ሰው ነበር። ሁለት ባልና ሚስቶች ግትር ከሆኑ በደስታ አብረው ሊኖሩ አይችሉም። ሁለት ግትር ሰዎችም ለረዥም ጊዜ ጓደኛሞች ሆነው መቀጠል አይችሉም።

አስታውሳለሁ አንዴ እስር ቤት ውስጥ ዳዕዋ አደርግ ነበር። ዳዕዋው የነፍስ ግድያ ወንጀል ለፈፀሙ እስረኞች ነበር። ስጨርስ አንድ እስረኛ ሊያመሰግነኝ ወደኔ መጣ። እስር ቤቱ ውስጥ የባህል ከፍል ኃላፊ ነው። ብዙዎቹን እስረኞች የግድያ ወንጀል ለመፈፀም ያነሳሳቸው ምን እንደሆነ ጠየቅኩት።

"ንዴት! ወላሂ ሸኽ ብዙዎቹ ግድያ የፈጸሙት ከሰዎች ጋር በትንሽ ነገር ተጣልተው ነው" ሲል መለሰልኝ። ከዚያም የታላቁን ነብይ ቃላት አስታወስኩ። "ጠንካራ ሰው ማለት ጠላቱን መሬት ላይ የሚዘርር ሳይሆን በቁጣ ወቅት ራሱን የሚቆጣጠር ነው።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

አዎ! ጀግና ማለት ጠንካራ ሰውነት ያለውና ታግሎ የሚያሸንፍ አይደለም። ይህ የጀግንነት መለኪያ ከሆነ ከሰዎች ይልቅ እንስሳት ይህ ብቃት አላቸው። ይልቁንም ጀግና ማለት የተለያዩ ሁኔታዎችን እንዳመጣጣቸው የሚያስተናግድ ብልህ ሰው ነው። ጀግና ማለት ሚስቱን፣ ልጆቹን፣ አለቃውንና የስራ ባልደረቦቹን በጥበብ የሚይዝ ሰው ነው።

"አንድ ዳኛ እየራበው ፍርድ መስጠት የለበትም" ይላል ሐዲሱ።(አቡ ዳውድ) ነብዩ (ሲ.ወ) ራሳችንን በታጋሽነት እንድናሰለጥን አዘውናል።

"ትዕግስት ከሆደ ሰፊነት ጋር ይመጣል" (ዳሩል ቁጥኒ)

አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ቁጣውን ሲቆጣጠር ስሜቱ መቶ ፐርሰንት ሊሆን ይችላል። በሁለተኛው ጊዜ ወደ ዘጠና በመቶ ይወርዳል። በሶስተኛው ጊዜ ወደ ሰማንያ በመቶ ይወርዳል። ሆደ ሰፊነት ሁለተኛ ተፈጥሮው እስኪሆን ድረስ።

ከጂዳ ከተማ በደቡብ በኩል ሶስት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው አምላጅ ከተማ ዳዕዋ እያደረግኩ እያለሁ ከቁጣ ጋር የተገናኘ አንድ ታሪክ ሰማሁ። ከታዳሚዎቹ መካከል በቀላሉ የሚቆጣ አንድ ወጣት ነበር። ይህ ወጣት በአንድ ወቅት በኖርማል ፍጥነት መኪና እያሽከረከረ ነበር። ከኋላው የቸኮለ የሚመስልና አልፎ መሄድ የሚፈልግ ባለ መኪና መጣ። ይህን የተመለከተው ወጣቱ ፍጥነቱን በጣም በመቀነስ መንገዱን ዘጋበት። ሰውዬው ትዕግስቱ ተሟጠጠ። ከወጣቱ መኪና ጋር እጅግ በጣም ተጠግቶ በአደገኛ ሁኔታ አለፈ። ወጣቱ ለምን አለፈኝ በሚል እሳት ሆነ። ከዚህ ያነሰ ነገር የሚያናድደው ሰው ነው። የቀደመውን መኪና መልሶ ለመቅደም ይሮጥ ጀመር። አልቻለም። አቁም በማለት ክላክስ ማድረግ ጀመረ። አቆመለት። ጥምጣሙን ወንበር ላይ አስቀምጠና መፍቻ ይዞ ወረደ። ወደ መኪናው ሲሄድ እሳት መልበሱ በግልፅ ይታይ ነበር። በድንገት ከዚያኛው መኪና ላይ ሶስት ጡንቻማ ጎረምሶች ዱብ ዱብ ብለው በመውረድ ወደሱ መጡ። መፍቻ ስለያዘ ድቢድብ መፈለጉን ተረድተዋል። ሲመጡበት ፈራ። እጁ ላይ ያለውን መፍቻ ወደ ላይ ከፍ አደረገና ይቅርታ ይህ መፍቻ ከናንተ መኪና ውስጥ እንደወደቀ ልነገራችሁ ብዬ ነው አላቸው። ተቀበሉትና መኪናቸው ውስጥ ገቡ። ቻው በማለት እጁን ያውለበልብላቸው ጀመር።

ስሌት...

ንዴት + ንዴት = እሳት



የልቦች ቁልፍ

እያንዳንዱ በር ቁልፍ አለው። የሰዎችን ልብ መክፈቻ ቁልፍ ስብዕናቸውን ማወቅ፣ ችግሮቻቸውን መፍታት፣ በመካከላቸው እርቅ መፍጠርና ከጥሩ ነገራቸው መጠቀም ከመጥፏቸው መጠበቅ ነው። አንድ ሰው የሰዎችን ስብዕና ማወቅ ከቻለ በነዚህ ሁሉ ጥበባት ዋና ይሆናል። ለምሳሌ በአንድ አባትና በልጁ መካከል ጠብ ተነሳ እንበል። በዚህም ምክንያት አባት ልጁን ከቤት አስወጣው። ልጅ ወደ ቤቱ ለመመለስ ቢፈልግም አባት አቋሙን ሊቀይር አልቻለም። አንተ ሁለቱን ልታስታርቅ ገባህ። ለአባት ይህን ጉዳይ የሚመለከቱ ኃይማኖታዊ ጉዳዮችን ነገርከው። ሊቀበልህ አልቻለም። በሂደት በጣም ስሜታዊ ሰው መሆኑን ተረድተሃል።

ስለዚህ የተለዩ አካሄድ መጠቀም አለብህ። "ለልጅህ እዘንለት እንጂ። አፈር ላይ ነው የሚተኛው። ፀሐይና ነፋስ ሌት ተቀን ያጣድፈዋል። አንተ እየበላህ እየጠጣህ እሱ በረሃብ እየተቆራመደ ነው። እንዴት ያስችልሃል? ምግብ በጎረስክ ቁጥር እሱ ትዝ አይልህም? ፀሐዩን ስታይ እሱን አታስታውሰውም? ህፃን እያለ ምን ያህል ትወደውና ትሳሳለት እንደነበር አስታውስ። አንተ አባቱ በህይወት እያለህ የአብራክህ ከፋይ የሆነው ልጅህ እንዴት ለምኖ ይብላ?" በለው። አባት በነዚህ ቃላት ተሸንፎ ለእርቅ ሲነሳሳ ታየዋለህ።

ሰውዬው ስስታም ከሆነ ደግሞ እንዲህ ልትለው ትችላለህ፡- "ወንድሜ ራስህን ለተጨማሪ ችግሮች ከመዳረግ ተቆጠብ። አታውቅም ይሄ ልጅ ሲርበው ሰዎችን ደብድቦ ንብረታቸውን ሊዘርፍ ይችላል። በዚህም የተነሳ ላደረሰው ጉዳት ፍርድ ቤት ካሳ እንድትከፍል ሊያዝህ ይችላል። ዞሮ ዞሮ አባት ነህ። የትም አታመልጥም። ስለዚህ ልጅህን አምጣና ሰብሰበህ ያዝ።"

አባት የፖንዘብ ኪሳራውን በመፍራት ተለሳልሶ ታገኘዋለህ። ልጅዬውን ሲታገግር ደግሞ ልጅ ሀብት አፍቃሪ ከሆነ እንዲህ ልትለው ትችላለህ፡- "አባትህ በጣም ያስፈልግሃል። ነገ ጠዋት ማግባትህ አይቀርም። ማን ነው የትዳር ወጪህን የሚሸፍንልህ? ብትታመም ማን ያሳከምሃል? ወንድሞችህ ከአባታቸው የኪስ ፖንዘብና ሰጦታ እየተቀበሉ ተንፈላሰው ተቀምጠዋል። አንተ ግን እዚህ ትሰቃያለህ። በእርግጥም አባትህን ግንባሩን ስመህ ይቅርታ አድርግልኝ ብትለው ሁኔታዎች ሁሉ ይቀየራሉ።"

በተመሳሳይ ባልና ሚስትን ለማስታረቅ ብትጠራ ተግቢውን ጥበብ በመጠቀም እርስ በርስ ልባቸውን እንዲከፍቱ ማድረግ ትችላልህ። ከስራ ገበታህ ላይ ፈቃድ ለመጠየቅ ከፈለግከና አለቃህ ለስራ እንጂ ለስሜታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ግድ የሌለው መሆኑን ካወቅክ እንዲህ ልትለው ትችላለህ፡-"ጉንካሬና ወኔ አገኝ ዘንድ ለሶስት ቀናት ያህል እረፍት ማድረግ እፈልጋለሁ። የስራ ብዛት ለጊዜውም ቢሆን ስራዬን በአግባቡ እንዳልወጣ አድርጎኛል። እባክህን አባትና እናቴ ጋር ልሂድና ትንሽ አረፍ ብዬ ተበረታትቼ ወደ ስራዬ እንድመለስ ፍቀድልኝ።" ለማህበራዊ ጉዳዮች በተሰይ ደግሞ ለቤተሰባዊ ጉዳዮች ትልቅ ትኩረት የሚሰጥ ከሆነ ደግሞ፡ - "አባቴንና እናቴን ለማየት ዕረፍት እፈልጋለሁ። ካየኋቸው ረጂም ጊዜ ሆነኝ። በጣም ናፈቁኝ" በለው።

እነዚህን ጥበባት አዳብር። ሰዎች ስላንተ እንዲህ እያሉ ሲያወሩ ትሰማለህ፡- "ሰዎችን በማሳመን ረገድ እንደሱ አይነት ጎበዝ ሰው አይተን አናውቅም። ጠይቆ እኮ አሳፍሮ የሚመልሰው ሰው የለም።"

ውጤት...

የእያንዳንዱ ሰው ልብ ቁልፍ አለው። የሰውየውን ስብዕና ማወቅ ትክክለኛውን መክፈቻ ለመለየት ይረዳል።



የሰውን ስነልቦናዊ ሁኔታ ከግንዛቤ አስገባ

በህዘንና በደስታ፣ በጤናና በበሽታ፣ በሀብትና በድህነት እንዲሁም በመረጋጋትና ባለመረጋጋት ወቅት የሰዎች ስሜት የተለያዬ ነው። ለአንድ ነገር የሚሰጡት ምላሽም እንዳሉበት ሁኔታ ይለያያል። አንድ ሰው በተረጋጋበትና ደስተኛ በሆነበት ወቅት ቀልድ መስማት ሊወድ ይችላል። በተናደደበት ወቅት ግን ይህ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ህዘን ላይ ላለ ሰው ቀልድ መቀለድ ተገቢ አይሆንም። ይሄው ቀልድ ግን በመዝናናት ላይ ላለ ሰው ቢነገር ጥሩ ይሆናል። ይህ ሁሉም ሰው በቀላሉ የሚረዳውና ማብራሪያ የማያስፈልገው ነገር ነው። ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ግን አንድ ሰው ሌላኛውን በሚያናግርበት ወይም በሚቀርብበት ጊዜ የሰውዬውን ስነ ልቦናዊ ሁኔታ፣ ስሜትና ስብዕና ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት የሚለው ነው።

አስቲ ከባሏ ጋር የተፋታችንና እናትና አባቷ የሞቱባትን ሴት እናስብ። ኢቃዎቿን ሰብስባ ወደ ወንድሟ ቤት ለመሄድ ትዘጋጃለች። በዚህ መሀል ጎረቤቷ ቻው ልትላት ትመጣለች። ተፋቺዋ ነገሩን ቀለል አድርጋ ያዬችው ለመምሰልና ወሬ ለማስቀየስ ብላ "ትናንት የሆነ ቦታ አይቼሻለሁ" ትላታለች። ጎረቤትዬዋም "አዎ! ባለቤቴ ውጪ ራት ካልጋበዝኩሽ አለኝና ወጣን። ከእራት በኋላ ለእህቴ ሰርግ የምለብሰው ቀሚስ ገዛልኝ። ከቀሚሱ ጋር አብሮ የሚሄድ የአንገት ሐብልም ገዝቶልኛል። ብታይው እንዴት እንደሚያምር? ወደ ቤት ስንመለስ ልጆቹ በጣም ተደብረው አገኘናቸው። አባታቸው አይዟችሁ ልጆቼ ቅዳሜና እሁድ አዝናናችኋለሁ ብሎ ቃል ገባላቸው።"

ምስኪኗ ተፋቺ ይህን ሁሉ እያዳመጠች ከወንድሟ ቤት ስትሄድ ምን እንደሚያጋጥማት ታስባለች። ጥያቄው ትዳሯ ለፈረሰባት ሴት የዚህን ዓይነት ወሬ ማውራት ተገቢ ነው ወይ? የሚለው ነው። ሴትዮዋስ ከዚህ በላይ ወሬዋን እንድትቀጥል ትፈቅድላታለች ወይ? ወደፊትስ ልታገኛት ትፈልጋለች ወይ? በጭራሽ አትፈልግም። ይልቁንም ልቧ በቅናትና በጥላቻ ይሞላል። ታዲያ መፍትሄው ምንድን ነው? በዘዴ ጥያቄዋን መመለስ ትችል ነበር። ለምሳሌ "አዎ አንድ ጉዳይ ነበረን። ለዚያ ወጥተን ነው" ካለች በኋላ ወዲያውኑ ርዕሷን ወደ መጣችበት ጉዳይ በማዞር የጎረቤቷን ችግርና ሐዘን ለማቃለል ትጥር ነበር። ለምሳሌ፡- ሁለት የሁለተኛ

ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ጓደኛሞች ለፈተና ተቀምጠው አንደኛው በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ውጤት ሲያመጣ አንደኛው በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ወድቆ ለዩንቨርሲቲ ትምህርት ሳያልፍ ቀረ።

ያለፈው ተማሪ ለወደቀው ጓደኛው ስላመጣው ውጤት፣ ስለ ዩንቨርስቲ ቆይታውና ወደፊት ስለሚጠብቁት ጥሩ ጥሩ ዕድሎች ማውራት ተገቢ አይደለም። ምንድን ነው ማድረግ ያለበት? የጓደኛውን ጭንቀት ስለሚያቀሉ አጠቃላይ ነገሮች ነው ማውራት ያለበት። የዩንቨርሲቲው ተማሪ በጣም ብዙ እንደሆነ፣ ከዛ ውስጥ አብዛኛው ተማሪ ከመመረቁ በፊት እንደሚባረር፣ ያንን ሁሉ አልፎ የተመረቀውም ስራ የማግኘት እድሉ አናሳ እንደሆነና ሌሎች የጓደኛውን ሀዘን የሚያቀሉ ነገሮችን ነው ማውራት ያለበት። ይህን ካደረገ ጓደኝነታቸው በጥሩ ሁኔታ ሊቀጥል ይችላል።

በተመሳሳይ ሁለት ጓደኛሞች አሉ። አንደኛው በገንዘብ የሚያንበሻብሸው ሀብታም አባት አለው። የሌላኛው አባት ግን የቤተሰቡን መሰረታዊ ፍላጎት እንኳ ለማሟላት የሚቸገር ነው። የሀብታሙ ልጅ ስለሀብቱና አባቱ ለሱ ገንዘብ መስጠት እንደሚወድ ለጓደኛው ማውራት የለበትም። ምክንያቱም ጓደኛውን ያሸማቅቀዋል። ራሱን እድለ ቢስ አድርጎ እንዲቆጥር ያደርገዋል። በዚህ የተነሳም ከዚህ ጓደኛው ለመራቅ ጥረት ያደርጋል። ለዚህ ነው ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሰዎችን ስነ ልቦናዊ ሁኔታና ደካማ ጎን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ላይ ትኩረት የሰጡት። "የሲጋ ደዌ በሽተኞችን አፍጥጠህ አትመልከት" ሲሉ ተናግረዋል። (ኢብኑ ማጃህ)

በሲጋ ደዌ በሽታ የተጠቃ ሰው የሰውነቱ ገፅታ ስለሚበላሽ ሰዎች ትኩር ብለው ሲመለከቱት ያለበትን የጤና ችግር እንዲያስታውሰና እንዲያዝን ያደርገዋል። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሰዎችን ደካማ ጎን እንዴት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ እንደነበር እንይ። መካን ለመቆጣጠር ጉዞ ላይ ነበሩ።

የአቡበከር (ረ.ዐ) አባት አቡ ቁሀፋህ አይነስውር አዛውንት ናቸው። ለልጃቸው ልጅ "ልጄ ሆይ! ወደ አቡ ቀይስ ተራራ ውሰጂን። ሙሐመድ ወደ መካ እየመጣ ነው እየተባለ የሚወራው ወሬ እውነት መሆኑን እንይ" አሏት። ወሰደቻቸውና "የሚታይሽን ነገር ንገሪኝ" አሏት። "ወደ እኛ እየቀረበ ያለ ጥቁር ነገር ይታየኛል" አለቻቸው።

እሳቸውም "ፈረሶች ናቸው" አሉ። በጥቁሩ ነገር ፊት ለፊት አንድ ሰው ወዲያና ወዲህ ሲል ይታየኛል አለቻቸው።

"ፈረሶቹን የመምራት ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው" አሉ።

"አሁን ጥቁሩ ነገር ተበታተነ" አለች። እሳቸው "ወላሂ ይሄ ማለት ፈረሶቹ መካ

ደረሱ ማለት ነው። ወደ ቤቴ በፍጥነት ውሰጂኝ። ቤቱን ዘግቶ የተቀመጠ ሰው ምንም አይሆንም ብለዋል" አሏት። ከተራራው ወርደው በመጓዝ ላይ ሳሉ ከሙስሊሙ ጦር ጋር ተገናኙ። አቡበከር አባታቸውን አግኝተው ሰላም አሏቸው። ከዚያም እጃቸውን ይዘው ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወሰዷቸው። ነብዩ ሲያይዋቸው አቡ ቁሃፋህ እርጅና አዳክሟቸዋል። አቡበከር አባታቸውን ተመለከቷቸው። ከተሊያዩ ብዙ ጊዜ ሆኗል። ኃይማኖታቸውን ለማገልገል ሲሉ ከቤተሰቦቻቸው ርቀዋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በርህራሄ "እኚህን አዛውንት ለምን ይዘሃቸው መጣህ እኔ ራሴ ሄጀ አልዘይራቸውም ነበር?" አሉ ለአቡበከር።

ጦር ሜዳ ላይ እንደነበሩና የጦር መሪውም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሆናቸውን ያውቃሉ አቡበከር። ብዙ ሰራዎች እንዳሏቸውም ያውቃሉ። ወደ አዛውንቱ ቤት ለመሄድ በቂ ጊዜ የላቸውም። አቡበከር ነብዩን አመሰገኗቸውና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርስዎ ከሚሄዱ እሱ ቢመጣ ይሻላል" ብዬ ነው አሏቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቡ ቁሀፋህን ፊት ለፊታቸው አስቀመጡና እጃቸውን ደረታቸው ላይ በማስቀመጥ "ኢስላምን ተቀበሉ" አሏቸው። የአቡ ቁሀፋህ ፊት በራ። "ከአላህ በስተቀር የሚገዙት ጌታ የለም። ሙሐመድ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ ናቸው" አሉ። አቡበከር በጣም ተደሰቱ። ነብዩ ሽማግሌውን ትኩር ብለው ተመለከቷቸው። ፀጉራቸው ነጭ ሆኗል። "ፀጉራቸውን አቅልምላቸው። በጥቁር ግን እንዳይሆን" አሉ። አዎ! ሰዎችን ሲቀርቡ ስነ ልቦናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ነበር።

በአርግጥ መካ በገቡ ጊዜ ጦሩን በብርጌድ በመከፋፈል የአንዱን ብርጌድ ባንዲራ ለጀግናው ሶሃባ ለሰዕድ ቢን ኡባዳህ (ረ.ዐ) ሰጡት። ባንዲራ መያዝ በጣም ትልቅ ክብር ነበር። ለያዥው ብቻ ሳይሆን ለህዝቦቹም።

ሰዕድ መካንና ነዋሪዎቿን ሲመለከት ነብዩን እንዴት እንደተዋጓቸው፣ እንዴት እንዳሰቃይዋቸው፣ እንዴት እንዳገለሏቸው፣ ሱመያንና ያሲርን እንዴት እንደገደሏቸው፣ ቢላልንና ኸባብን እንዴት እንደገረፏቸው አስታወሰ። ትምህርት ሊያገኙ እንደሚገባም አሰበ። ባንዲራውን እያውለበለበ "ዛሬ የእርድ ቀን ነው። ዛሬ የናንተ አይነኬዎች ሁሉ ጥቃት ይደርስባቸዋል" አለ። ይህ ለቁረይሾች ከባድ ነገር ነው። ሁላችንንም ሊጨርሰን ይችላል ብለው ፈሩ። አንዲት ሴት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በፍጥነት ሄደችና በግጥም ሰዕድን የሰው ደም ከማፍሰስ እንዲከለክሉት ለመነቻቸው።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በግጥማዊ ቃላቱ ተደመሙ። ጉዳዩም አሳዘናቸው። ሆኖም የሰጡትን ክብር በመንጠቅ ሰዕድን ሊያስቀይሙት አልፈለጉም። ባንዲራውን ለልጁ ለቀይስ ቢን ሰዕድ እንዲሰጠው አዘዙት። መካ ሲገቡ ሰዕድ ፈረስ እየጋለበ ነበር። ሴትዮዋ ባንዲራ አለመያዙን ስታይ ተደሰተች። ሰዕድ አሁንም የብርጌድ መሪ



ለሰዎች አስብ

ሰዎች ዋጋ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ። ለዚህ ነው ግለሰቦች የሌሎችን ትኩረት ለማግኘት ሲሉ የሆነ ዓይነት ባህሪ ሲያሳዩ የሚስተዋለው። ትኩረት እንዲሰጧቸው ወይም እንዲገረመላቸው በማሰብም የጀግኖቻቸውን ተረቶች ወይም ታሪኮች ሊፈጥሩ ይችላሉ።

አንድ ደከሞት ከስራ ወደ ቤቱ የሚገባን ሰው እንመልከት። ወደ ሳሎን ሲገባ አራቱም ልጆቹ ብቻቸውን ተቀምጠዋል። የመጀመሪያ ልጁ አስራ አንድ ዓመቱ ሲሆን ቴሌቪዥን ያያል። ሁለተኛው ልጅ ራቱን እየበላ ነው። ሶስተኛው በአሻንጉሊቶቹ ይጫወታል። አራተኛው የቤት ስራውን ይሰራል። አባት ድምፁን ከፍ አድርጎ "አሰላሙ አለይኩም" አላቸው። አንደኛው ልጅ ቴሌቭዥን ላይ በሚያየው ነገር ተመስጧል። ሁለተኛው ልጅ ፀጥ ብሎ ራቱን ይበላል። ሶስተኛው ከአሻንጉሊቶቹ መለያየት አልቻለም። አራተኛው ልጅ አባቱን ሲያይ መፅሐፎቹን ወርውሮ በደስታ ወደ አባቱ ሮጠ። እጁን ሳመውና ወደ መፅሐፉቱ ተመለሰ። ከአራቱ ልጆች በአባቱ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ የሚሆነው የትኛው ነው? ምላሻችን ተመሳሳይ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። አራተኛው ልጅ ነው። ቆንጆ ስለሆነ አይደለም። ጎበዝም ስለሆነ አይደለም። ለአባቱ ዋጋ ስለሰጠ ብቻ።

አንድ ሰው ለሌሎች በተጨነቀ ቁጥር እነሱም ለሱ ያላቸው ፍቅርና ክብር ይጨምራል። ከፍጥረታት ሁሉ የበላይ የሆኑት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሰዎች ላይ እነዚህን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ነበር። ሰዎች ጭንቀታቸው የነብዩ ጭንቀት ችግራቸው የነብዩ ችግር ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጉ ነበር።

አንድ ቀን ኹጥባ ለማድረግ ወደሚንበራቸው እየወጡ ሳለ አንድ ሰው ወደ መስጊድ ገባ።

የአላህ መልዕክተኛ! አለና ስለኃይማኖቱ ይጠይቃቸው ጀመር። ብዙ እውቀት አልነበረውምና። ነብዩ ሲመለከቱት ኹጥባው እስኪያልቅ ድረስ ሊታገስ የማይችል ገጠሬ ነው። ድጋሚም መስጊድ ላይመጣ ይችላል። ጉዳዩ ለሰውዬው በጣም አንገብጋቢ ነው። ለዚህም ነው ኹጥባውን አቋርጠ ጥያቄ የጠየቃቸው። ነብዩ የሚያስቡት ከራሳቸው አንፃር ሳይሆን ከሰዎች አንፃር ነው። ከተከበረው ሚንበራቸው በመውረድ ወንበር እንዲመጣላቸው አዘዙና ከሰውዬው ፊት ለፊት ተቀመጡ። ከዚያም እስኪገባው ድረስ ለጥያቄው መልስ ሰጡት። ኹጥባቸውን